# የዜጎች መድረክ

ኢዜማ

ቅፅ 1 ቁጥር 57 መስከረም 27 ቀን 2013ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ


# ስንብት ለጋሸ መስፍን

በብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)



# ስንብት ለጋሽ መስፍን

## በብርሃኑ ነጋ(ፕሮፌሰር)



ብዙ ጊዜ በሀገራችን እንዲህ አይነት የክብር አሸኛኘት የሚደረገው በተለይ በስልጣን ላይ ለነበሩ፤ ለሀገራቸው በጦር ሜዳ ላይ ትልቅ ጀብዱ ፈጽመው ላለፉ፤ ወይንም ደግሞ በማኅበረሰቡ ባህል ዙሪያ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረጉ ዘፋኞች ወይንም የአገርን ስም በስፖርት ላስጠሩ ሯጮች ነው። ዛሬ የምንሸኘው ይህ ትልቅ አዛውንት ጋሽ መስፍን (በህይወቱ አንተ ስለው የነበረን ሰው በሞቱ አንቱ ለማለት ስለከበደኝ ነው) በነኝህ መስኮች እምብዛም ታዋቂ የነበረ ሰው አይደለም። በስፖርቱ በጣም ብዙ የሚኮራበት የእግር ኳስ ጨዋታም ቢሆን ጥሩ ተርሲኒ ከመሆን ያለፈ ሀገራዊ ስም የሚያሰጠው ዝና አልነበረውም። ሙዚቃ ላይም እኔ እስከማውቀው ሙዚቃ ይወዳል እንጂ ራሱን ለታዋቂ ዘፋኝነት የሚያበቃ ድምጽ አልነበረውም። ጥሩ ኮሜዲያን እንዳይሆን ቀልዱን መናገር ጀምሮ እስከሚጨርስ በራሱ የተለየ ያሳሳቅ ስልት ስቆ፤ ባሳሳቁ ሌላውን ያስቅ እንደሆን እንጂ ሌላውን የማሳቅ ችሎታ እምብዛም አለው ለማለት ያስቸግራል።

በርግጥ ሀገራችን ካፈራቻቸው ትላልቅ ምሁራን አንዱ ነው ጋሽ መስፍን። ከሙያው ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ዙሪያ ብዙ ጽሁፎችን አበርክቶልናል። ግን እኔ እስከማውቀው ድረስ በሀገራችን ብዙ ከጋሽ መስፍን ያልተናነሱ ምሁራን አልፈዋል። በዚህ ደረጃ ግን ክብር ሰጥተን የሸኘናቸው ብዙ ያሉ አይመስለኝም። ጋሽ መስፍንን ምናልባት ከሌሎቹ ምሁራን የተለየ የሚያደርገው፣ ሁሌም የጥናቱ ማጠንጠኛ ኢትዮጵያ መሆኗና ለባለሙያተኞች ስብሰባዎች የሚያቀርባቸው ጥናታዊ ጽሁፎች ወይንም ባደባባይ ለሕዝብ የሚያቀርባቸው አጫጭር ሂሳዊ ጽሁፎች ሁሌም ኢላማቸው አንድ እሱ የሀገር ችግር ነው ብሎ የሚያስበውን ጉዳይ (ያጭር ጊዜም ሆነ የረጅም ጊዜ) ለመፍታት ኢላማ ያደረጉ ጹሁፎች ናቸው። ዝም ብሎ መሬት ያልረገጠ አካዳሚያዊ ክርክር ሳይሆን ቀልቡን የሚስበው፤ ከዚህች ሀገር ጋር በቀጥታ የተያያዙና እሱን የሚያብሰለስሉት ጉዳዮች (የሀገሪቱ አስከፊ ድህነትና ኋላ ቀርነት፤ የዜጎች/የሰዎች መብት፤ ያገዛዝ ሥርዓቶች በማኅበረሰቡ አባላት ነጻነት ላይ በሚያስከትሏቸው ተጽእኖዎች ዜጎች ሁሌም መንግሥትን እንደፈሩና አንገታቸውን እንዳቀረቀሩ የሚኖሩበት ሁኔታ ለዘለቄታው በማኅበረሰቡ ስነልቦናም ሆነ ይበልጡንም ደግሞ በአንድነቱ ላይ የሚደቅኗቸው አደጋዎች...ወዘተ) ናቸው እሱን ሁል ጊዜ የሚያሳስቡትና ብእሩን እንዲያነሳ የሚገፋፉት። በዚህም ምክንያት ጋሽ መስፍን ከሀገሩ ከኢትዮጵያ ጋር በጣም የተወሳሰበ ግንኙነት ነበረው። ሀገሩን ክፉኛ ይወዳል፤ ግን የዚያን ያክል ደግሞ በሀገሩ ላይ የሚያየው ቅጥ የለሽ ድህነት፤ ፍትህ ማጣት፤ የዜጎች ነጻነት ማጣትና “በፍርሀት ቆፈን” ተይዞ መኖር ሁሌም ያመዋል።

እንዲህ አይነት በሀገር ፍቅር ባንድ በኩልና፤ በሀገር ዘርፈ ብዙ ውድቀት በሌላ በኩል ምክንያት ነፍሳቸው የምትዋዥቅባቸው ብዙ ኢትዮጵያውያን እንዳሉ እናውቃለን። ብዙዎቹ እነኝህን የውስጥ ግጭቶች በየቤታቸው ወይንም ከጥቂት ጓደኞቻቸው ጋር ይነጋገሩበት እንደሆነ እንጂ በግላጭና በአደባባይ ከማኅበረሰቡ ጋር ለመነጋገር “ይፈራሉ”። ይህንን እውነታ ለመቀየር ምንም ነገር ሳያደርጉ “ጥሩ ኑሮ” ኖረው ይሞታሉ። እዚህ ላይ ነው ጋሽ መስፍን በግልጽ ከሌሎች እንደሱ “ምሁራን” ከሚባሉት የሚለየው። ለሱ ሀገርን የሚያክል ትልቅ ጉዳይ የሚመለከት ነገር፤ በሀገርና በሕዝብ ሀብት የተማሩ “ምሁራን” ዝም ብለው በየጓዳውና በየማኅበሩ ለመብላት ሲገናኙ የሚያወሩትና የሚያሙት ነገር ሳይሆን፤ የተበላሸውን ለማስተካከል በግላጭ ከሚመለከተው አካል ጋር (የመንግሥት ስልጣንን ከያዘው አካል ጭምር) በአደባባይ የመናገር የሞራል ድፍረቱ ሊኖራቸው ይገባል የሚል ጽኑ እምነት ስለነበረው፤ ይህን እምነቱን ደግሞ በተግባር ለማሳየት መቻሉ ነው እሱን በተለየ ሁኔታ እንድናየውና እንድናከብረው የሚያደርገን። ጋሽ መስፍን በዘመኑ ለነበሩት የትምህርት እኩዮቹ ብቻ ሳይሆን ከሱም እድሜ በብዛት ለሚያንሱት ቀጣይ ትውልዶች ይህንን የሞራል እዳ እንዲሸከሙ ስለሚያስገድዳቸው ነው በተለይ በእድሜ የሚጠጉትና እነሱ በተለያየ የቁሳዊ ሕይወት ግፊት ምክንያት የሀገሪቱን መከራ ከዳር ቆመው ለሚያዩት ሁሌም የሱ ግልጽነትና ድፍረት የሚጎረብጣቸው።

ከዚህ አንጻር ዛሬ ልንሸኘው የተሰባሰብነው ይህ ሰው፤ ቢያንስ ላለፉት ሶስትና አራት ትውልዶች የማኅበረሰባችን የሞራል ኩራዝ ሆኖ ያገለገለ ትልቅ ሰዋችን ነው። ይህንን ሚናውን የተወጣው በድንገት ሳይሆን አውቆ ነው። እንዲህ አይነት አስቸጋሪ ሚና ከተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ትችትን፤ ስድብን ውግዘትን ሊያስከትል እንደሚችል ማወቅ ብቻ ሳይሆን እንደማይቀርለት አውቆ የገባበት ጉዳይ ነው። በአገዛዝ ስርአቶች ታስሮበታል፤ በጊዜና በተውሶ እውቀት ልቀናል በሚሉ ወጣት አብዮተኞች ተዘልፎበታል፤ ከብሔርህ ውጭ ለምን “ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ ትላለህ” በሚሉ አዳዲስ የጎሳ ብሄረተኞች ተንጓጦበታል። ሁሉም በሀሳብ ሊሞግቱት ከፈለጉ ሁሌም ለመወያየት ክፍት ነበር። ሀሳብን በሀሳብ መሞገት አቅቷቸው ወደ ስድብና አካኪ ዘራፍ ለሚሄዱ ምንም ፍርሀትም ክብርም የለውም። በተለይ ለማኅበረሰባችን የሞራልና የእውቀት ልቀት ኃላፊነት ያለባቸው አካላትና ግለሰቦች ለንዋይ/ለስልጣን ብለው ኃላፊነታቸውን ሳይወጡ ሲቀሩ ፍጹም ይጠየፋቸዋል። ከኢትዮጵያውያን ዜጎች እንደ ዜጎች ውጭ በተለየ የሚወደው ብሔር የለም። ለማንኛውም ለተበደለ ኢትዮጵያዊ ዘርና ኃይማኖት ሳይለይ በአደባባይ ጥብቅና ቆሟል። ሁሌም ወገንተኛነቱ አቅም ለሌላቸው ኢትዮጵያዊ ወገኖቹ ነበር። ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲና ሰብዓዊ መብት ከልቡ ታግሏል። እኔ እስከማውቀው ድረስ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ጥቅም በሚመለከት ማድረግ እያለብኝ ያላደረግኩት ነገር አለ ብሎ የሚቆጭበት ምንም ነገር ያለ አይመስለኝም። በሱ መሞት እኔ የምቆጨው ብዙ የደከመበትን የኢትዮጵያን ዴሞክራሲ ሳያይ በማለፉ ነው። ያ ምኞትህ እንዲሳካ ከልባችን እንደምንሞክር ቃል እገባልሀለሁ።

ጋሽ መስፍን የኖረው ኑሮና ህይወቱ ለማህበረሰባችን ትቶ የሚያልፈው ትምህርት በተለይ ለወጣቱ ትውልድ እውነት፤ ፍትህ፤ ላመኑበት መቆም፤ ለአላፊ ቁስም ሆነ ለስልጣን አለማጎብደድ/አለመሸነፍ፤ ዝም ብሎ ጎርፉ በሚሄድበት መሄድ ሳይሆን በሁለት እግር ቆሞ ለራስ ማሠብንና ባመኑበት መቅዘፍን፤ ምንም እንኳን ንዋይ ባያስገኝ በማኅበረሰብ ዘንድ በጣም የሚያስከብር የማኅበረሰብ እሴት መሆኑን ለዚህ ሰው ሕብረተሰባቸን በሰጠው ክብር ታያላችሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ባጠቃላይ የማኅበረሰባችን የሞራል ቁመና እጅግ በተዳከመበት በዚህ ጊዜ የጠንካራ የሞራል ቁመናን አስፈላጊነት በህይወቱ ብቻ ሳይሆን እንዲህ በሞቱ በሰጠነው ክብር ለምታዩ፤ የሞራል ልዕልና ለማኅበረሰብ ሰላምና ጤንነት ምን ያክል አስፈላጊ እንደሆነ ታያላችሁ ብዬ እገምታለሁ።

ስሞት አታልቅሱ፤ ስሞት አትቅበሩኝ ይልቁንስ አስከሬኔን አቃጥላችሁ አመዴን አዋሽ ላይ በትኑት ብለሀል፤ በህይወቴ ያልገዛሁትን መሬት ለሞቴ እንዲኖረኝ አልፈልግም ብለሀል፤ ይህ ፍላጎትህ በሞትህ መሳካቱን አላውቅም፤ በህይወትህ ግን የምትፈልገውንና የምታምንበትን ኖረሀል። ይህን ስንታችን ደረታችንን ነፍተን እንለዋለን? መልካም እረፍት ጋሽ መስፍን፤ አንረሳህም።


# አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች
ለማኀበራዊ ፍትህ
(ኢዜማ)

መስከረም 27 ቀን 20113 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ቆይታ

## ‹‹የሠራተኛውን ምንዳ እየወሰዱ ለሠራተኛው ትንሽ ገንዘብ የሚሰጡ ድርጅቶች፣ የሠራተኛውን መብት እየጣሱ ስለሆነ ኢዜማ ከሠራተኞቹ ጎን ይቆማል››

ወንድወሰን ተሾመ የኢዜማ ሙያ ማኅበራት ተጠሪ

የዛሬው የዜጎች መድረክ የቆይታ አምድ እንግዳ የኢዜማ ሙያ ማኅበራት ተጠሪ የሆኑትና በቅርቡ የብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ሆነው የተመረጡት ወንዶሰን ተሾመ ናቸው፡፡ በተጠሪነት የሚያገለግሉት ሙያ ማኅበራት ኮሚቴ ምን ሲሰራ እንደነበር? ምን ለመስራት እንዳቀደና ሙያ ማኅበራት ሚና ምን ሊሆን ይገባል? በሚሉ ነጥቦች ዙሪያ አጠር ያለ ቆይታ አድርገናል፡፡ እንድታነቡት አንጋብዛለን፡፡ መልካም ንባብ!

*የሙያ ማኅበራት ቋሚ ኮሚቴ ባሳለፍነው የ2012 ዓ.ም ምን ሲሰራ ነበር? በያዝነው የ2013 ዓ.ምስ ምን ለመስራት አቅዷል?*

በኢትዮጵያ ፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ማንኛቸውም ፓርቲዎች የሙያ ማኅበራት የሚባል ዘርፍ በሥራ አስፈፃሚ ውስጥ ውክልና እንዲኖራቸው አድርገው አያውቁም፡፡ ኢዜማ ለሠራተኞች የሚቆም መሆኑን ለማመላከት በሥራ አስፈፃሚ ደረጃ ሁለት ሰዎች ውክልና እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡ በ2012 ዓ.ም የሙያ ማኅበራት ቋሚ ኮሚቴ ካቋቋምን በኋላ የቋሚ ኮሚቴውን ደንብና ሥርአት እንዲቀረፅ አድርገናል፡፡ ዓመታዊ እቅዳችንንም ነድፈናል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ 23ቱም ወረዳዎች ውስጥ የሙያ ማኅበራት ዘርፍ ተጠሪዎች ስልጠና በመስጠት እንዲዋቀሩ አድርገናል፡፡ የተለያዩ የሙያ ማኅበራትን በመጋበዝም በሰሜን ሆቴል ውይይት አካሄደናል፡፡

በ2013 ዓ.ም በቋሚ ኮሚቴያችን ውስጥ ያሉትን ሰባት አባላት ወደ ዘጠኝ በማሳደግ በሙያ ዘርፎቻቸው ደልድለናል፡፡ ዓመታዊ በጀታችንንና የስልጠና ግብአቶቻችንንም አዘጋጅተን አቅርበናል፡፡ የምርጫ ግብረ ሀይል ብሔራዊ ኮሚቴ ውስጥ ከወጣቶችና ከሴቶች ጋር አብረን እየሰራን እንገኛለን፡፡ የምርጫ ግብረ ሀይሉ በምርጫ ሂደት ውስጥ የተለያዩ ሥራዎችን ስለሚከውን በእኛ ዘርፍ ውስጥ ሰዎች እንዲመለመሉ ዝግጅት እያደረግንም ነው፡፡ የሙያ ማኅበራት ቋሚ ኮሚቴ በአዲስ አበባ በሚገኙ 23ቱንም ወረዳዎች በማሰልጠን ታች ድረስ ስልጠና እንዲሰጥ ቡድን አሰማርተን እየተንቀሳቀሰን እንገኛለን፡፡

*በርካታ ሙያ ማኅበራት በሀገራችን እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ቀደም ብሎ የነበረው የመያዶች አዋጅ የሙያ ማኅበራቱን የሚያሰራ እንዳልነበር ሲገለፅ ቆይቷል፡፡ ለውጥ መጣ ተብሎ ከተገለፀ በኋላ ያለው አዋጅ አሰሪ ነው? ይህንን ለመፈተሽስ ሙከራ አድርጋችኋል?*



መንግሥት፣ የሙያ ማኅበራት የመንግሥት አገልጋይ ብቻ ሆነው ነው እንዲንቀሳቀሱ ሲያደርግ የነበረው፡፡ የሙያ ማኅበራት መሪዎችም የስርአቱ ካድሬዎች ናቸው፡፡ ጥብቅና የሚቆሙትም ለሠራተኛው ሳይሆን ለመንግሥት ነው፡፡ ያለፈውን ጊዜ ስንመለከተው ተስፋ የሚደረግበት አልነበረም፡፡

2011 ዓ.ም ላይ የታወጀው የአሰሪና የሠራተኞች አዋጅ ካለፈው የተሻሻለ ነው፡፡ ከ2011 ዓ.ም ወዲህ መደራጀት ላይ እቀባ እየተጣለ አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር ለውጥ አለ፡፡

ሆኖም በግል ትምሕርት ቤት የሚያስተምሩ መምሕራኖች አልተደራጁም፡፡ በአሰሪና በሠራተኞች ሕግ መሰረት እየተዳደሩ አይደለም፡፡ የሕብረት ስምምነት የላቸውም ፡፡ የትየለሌ ቁጥር ያለው መምሕር ነው ያልተደራጀው፡፡ ሌላው አሳሳቢ የሆነው ነገር የሠራተኞችን ደሞዝ እየወሰዱ የሚያስቀጥሩ ደርጅቶች መኖር ነው፡፡ እነዚህ ድርጅቶች ለሠራተኛው ትንሽ ደሞዝ ይከፍሉና አብዛኛውን ገንዘብ ራሳቸው ነው የሚወስዱት፡፡ ይህን መሰል ሥራ የሚሰሩ አስቀጣሪ ድርጅቶች በሠራተኞች ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያስከተለ ነው፡፡ እኛም ይህንን ጉዳይ እንደ አጀንዳ ይዘን ለመነሳት አቅደናል፡፡ ያልተደራጁ በተለያዩ መሥሪያ ቤቶች የሚሰሩ መምሕራን ተደራጅተው በአሰሪና ሠራተኛ የሕብረት ስምምነት ደንብ መሰረት የሚተዳደሩበትን መንገድ እንዲፈጥሩ ግፊት ለማድረግ ዝግጅት ላይ ነው ያለነው፡፡

የእኛ ዓላማ በየሙያ ማኅበራቱ በመግባት የሙያ ማኅበራትን ሥራ መከወን አይደለም፡፡ የእኛ አላማ የእነሱን አላማ ሊያስፈፅም የሚችል ገዢ ሀሳብ የያዘ ፓርቲ እንዲለዩ ማድረግና ያ ፓርቲ እንዲመረጥ ግፊት እንዲያደርጉ ማገዝ ነው፡፡

*የኦሮምኛ ቋንቋ በሚያስተምሩ ትምሕርት ቤቶች በሚመለከት ከምክትል ርዕሰ መስተዳድር ቅጥር ጋር በተያያዘ አንድ ውዝግብ ተነስቶ ነበር፡፡ እርስዎ የሚመሩት የሙያ ማኅበራት ኮሚቴ ከዚህ ጉዳይ ጋር ተገናኝቶ ሲነሳ የነበረውን ውዝግብ ፈትሾታል? ፈትሾት ከሆነስ ምን ውጤት አገኘ?*

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኙ ምክትል ርዕሰ መምሕራን በሙሉ ኦሮሞዎች ሊሆኑ ነው የሚል ወሬ ተናፍሶ ነበር፡፡ ይህንን ለማጣራት ወደ ኢትዮጵያ መምሕራን ማኅበር (ኢመማ) አቅንቼ ነበር፡፡ ኢመማ ካቀናሁ በኋላ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ የሆኑትን ጫንያለውን ማግኘት ችዬ ነበር፡፡ የአዲስ አበባ የሰው ሀይል ቢሮ ያዘጋጀውን ባለ 26 ገፅ ሰነድ ነበር ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው የሰጡኝ፡፡ በሰነዱ ላይ እንደተመለከትኩት በአዲስ አበባ ውስጥ በጥምርና በቅንጅት ኦሮምኛ በሚሰጥባቸው ትምሕርት ቤቶች በአንደኛ ደረጃም ሆነ በሁለተኛ ደረጃ ካሉ ከሶስቱ ርዕሰ መምሕራን መሀከል አንዱ ኦሮሚፋን ማንበብ፣ መፃፍና መናገሩ በፈተና ይረጋገጣል ይላል፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ የአዲስ አበባ መምሕራን ማኅበር ሊቀመንበር ጋርም ተነጋግሬያለሁ፡፡ ከፍተኛ የሆነ የመምሕራን ጥያቄ እንዳለና በዚህ መልኩ (ኦሮሚፋ መናገር የሚችሉ መምሕራን ብቻ ይመለመላሉ) ምልመላው ይካሄዳል የሚል ፍራቻ እንደነበር ገልፆልኛል፡፡ መጨረሻ ላይ የተገነዘብነው ነገር ቢኖር በአዲስ አበባ ሶስት አይነት ትምሕርት ቤቶች እንዳሉ ነው፡፡ አንደኛው ሙሉ ለሙሉ አማርኛ ቋንቋ ብቻ የሚሰጥባቸው ትምሕርት ቤቶች ናቸው፡፡ ይሄ ጉዳይ እነሱን አይመለከታቸውም፡፡ ሁለተኛው በቅንጅት የሚሰጡ ትምሕርት ቤቶች እንዳሉ ነው፡፡ በቅንጅት (ኦሮሚፋም አማርኛም አንድ ላይ የሚሰጡበት) በሚሰጡ ትምሕርት ቤቶች ውስጥም ብዙ የኦሮሚፋ ተማሪዎች ያሉበት አይደሉም፡፡ ቁጥራቸው አነስተኛ ለሆኑት ተማሪዎች ነው አንድ ርዕሰ መምሕራን እንዲኖር የሚደረገው፡፡ ሁለቱ የቋንቋ ትምሕርቶች በሚሰጡበት ጊዜም የቋንቋ ትምሕርቱ ቅቡልነት ያለበት እንዲሆንና ኦሮምኛ ቋንቋ አፍ መፍቻቸው የሆኑ ሰዎች አማርኛ እንዲማሩ በተመሳሳይ አማርኛ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው የሆኑ ሰዎች ኦሮምኛ እንዲማሩ የማሳመን ሥራ በትምሕርት ቢሮ አልተሰራም፡፡ ይህ ስህተት ነው፡፡ በኦሮሚያ ክልል ለምሳሌ 5ኛ ክፍል ሲደርሱ ነው ተማሪዎች አማርኛ እንዲማሩ የሚደረገው፡፡ እንግሊዘኛ ቋንቋን ግን ከ1ኛ ክፍል ጀምሮ ነው እንዲማሩ የሚደረገው፡፡ ይህ ትልቅ ስህተት ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ሁለቱ ቋንቋዎች በቅንጅት በሚሰጡባቸው ትምሕርት ቤቶች ውስጥ ያለው መንፈስ ጤናማ እንደማይሆን ተገንዝበናል፡፡

በ5 ክፍለ ከተሞች የሚገኙ 9 የወረዳ ፅ/ቤቶችን ጎብኝተናል፡፡ ከእነሱ እንደተረዳነው የወረዳው ኃላፊ ለማያውቀው ሰው ለአንደኛ ደረጃ ትምሕርት ቤት 10 በመቶ ነጥብ ይሰጣል፡፡ ለማያውቀው ሰው ነው ይህን ነጥብ የሚሰጠው፡፡ ክፍለ ከተማው ደግሞ 10 ነጥብ ይሰጠዋል፡፡ 20 ነጥብ በቀጥታ አገኘ ማለት ነው፡፡ እነዚህ 20 ነጥብ የሚያገኙ ተወዳዳሪዎች ነጥቡን የሚያገኙት መንግሥት የሚፈልጋቸው ብቻ ስለሚሆኑ እንቅፋት ይሆናሉ የሚል ቅሬታ ነው ያቀረቡልን፡፡ ኦሮሚያ የነበሩ ርዕሰ መምሕራን ከኦሮሚያ በተሞላላቸው መመዘኛ ነጥብ ከኦሮሚያ መጥተው ሊወዳደሩ ነው የሚለው ወሬ ግን ፍፁም ስህተት ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ ተጨማሪ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እንቅፋት የሆነብን ሌላው ጉዳይ ቢኖር መምሕራን ወደ ት/ቤት እየመጡ አለመሆን ነው፡፡ ትምሕርት ቤቶች ሲከፈቱ መምሕራንን ስለምናገኛቸው ይህንን ጥያቄ መልሰን እንፈትሸዋለን፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ ግን በማኅበራዊ ሚድያው እንደተናፈሰው ወሬ ሳይሆን ቀደም ብዬ ባነሳሁት መልክ ነው ሲሰራ የነበረው፡፡ ጉዳዩን አጣርተን ከጨረስን በኋላም ለብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሪፖርት የምናደርግ ይሆናል፡፡

*ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመገንባት በሚደረገው ሂደት ውስጥ ሙያ ማኅበራት የሚጫወቱት ሚና ምንድነው ይላሉ?*

ለአንዲት ሀገር ዴሞክራሲያዊ ስርአት እውን መሆን አንዱ የዴሞክራሲ ተቋማት መበልፀግ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሙያ ማኅበራት መበልፀግ፣ መደራጀትና ተፅዕኖ ፈጣሪ መሆን ነው፡፡ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ተፅዕኖ ያሳደሩ ስብስቦች መሪዎች ብንመለከትም ከመምሕራን ማኅበር ወይም ኢሠማኮ አባል ሆነው ነው የምናገኛቸው፡፡ በ1997 ዓ.ም በተደረገው ምርጫም ትልቅ ሚና ነበራቸው፡፡ የሙያ ማኅበራት መኖር ለዴሞክራሲያዊ ስርአት መኖር ትልቁን ሚና ነው የሚጫወቱት፡፡ ኢዜማም ይህንን ስለተረዳ ነው ይህንን ዘርፍ አቋቁሞ እየተንቀሳቀሰ ያለው፡፡

*በኢትዮጵያ በስፋት የሚታየውን ዘውግን መሰረት አድርጎ የተንሰራፋውን ፖለቲካ ሙያ ማኅበራት ማረቂያ መንገድ ሊያበጁለት ይችላሉ በሚል አስተያየታቸውን የሚሰነዝሩ ወገኖች አሉ፡፡ ይህንን አስተያየት እንዴት ይመለከቱታል? እውነትስ በዘውግ ፖለቲካ ለተሞላው ፖለቲካ ማረቂያ መንገድ ሊያበጁ ይችላሉ?*

የዘውግ ፖለቲካ ለሙያ ማኅበራት ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያም የሚጠቅም አይደለም፡፡ ከ1984-1997 ዓ.ም ያለውን የኢትዮጵያ መምሕራን ማኅበር ታሪክ ስንቃኝ አንድ አብይ ስህተት እናገኛለን፡፡ አብዩ ስህተት መምሕራን ማኅበሩ በዘውግ እንዲደራጅ መደረጉ ነው፡፡ የኦሮሚያ፣ የሲዳማ፣ የአማራ ወዘተ... እየተባለ እንዲደራጅ ተደርጓል፡፡ ይህን አደረጃጀት በመጠቀምም የየክልሉን መምሕራን የእረፍት ጊዜ በተለያየ ወቅት እንዲሆን አድርገዋል፡፡ በወቅቱ እኛ ለሙያ ማኅበራት ትግል የምናደርገው እያስተማርን ነበር፡፡ ስብሰባዎች ላይ እንዳንገናኝ ትምሕርት ቤቶች ክፍት እንዲሆን ይደረጉ ነበር፡፡ ለምሳሌ ኦሮሚያ ክፍት ሲሆን አዲስ አበባ ዝግ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ አዲስ አበባ ክፍት ሲሆን ኦሮሚያ ዝግ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ የመምሕራንን እረፍት በዚህ መልኩ በማፈራረቅ እንዳንገናኝና ትግል እንዳናደርግ እንቅፋት ሲፈጠርብን ነበር፡፡

ሙያ ማኅበራት ውስጥ አባል ስትሆን የመምረጥም ሆነ የመመረጥ መብት ሊከበር ይገባል፡፡ በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ሙሉ ተሳታፊ መሆን ሊከበር ይገባል፡፡ መምረጥ እንጂ መመረጥ አይቻልም፡፡ ይህ ደግሞ የሆነው መመዘኛው ዘውግ በመሆኑ ነው፡፡ ዴሞክራሲን ሊያበለፅጉ በሚችሉ ተቋማት ላይ በብሔር መታጠርና በዘውግ ተደራጅ ማለቱ ጎጂ እንጂ ጠቃሚ አይደለም፡፡ የሙያ ማኅበራት አባል ለመሆን ሰው መሆን ብቻ በቂ ነው፡፡ በዘር ከረጢት ታቅፎ አባል መሆን መብት ማስገፈፍ ነው፡፡

*መነሳት ሲኖርበት አልተነሳም የሚሉት ጉዳይ ካለ? ወይም የሚያስተላልፉጥ ጥሪ ካለ እድሉን ልስጥዎትና ቆይታችንን እንቋጨው፡፡*

በጣም አመሰግናለሁ፡፡ ጥያቄዎቹም ጥሩ ነበሩ፡፡ አንድ መልዕክት ማስተላለፍ እፈልጋለሁ፡፡የሠራተኛውን ምንዳ እየወሰዱ ለሠራተኛው ትንሽ ገንዘብ የሚሰጡ ድርጅቶች፣ የሠራተኛውን መብት እየጣሱ ስለሆነ ኢዜማ ከሠራተኞቹ ጎን እንደሚቆም ልገልፅ እፈልጋለው፡፡ ይህንን በማስመልከት ባላችሁበት ቦታ ሆናችሁ ለእኛ ሪፖርት እንድታቀርቡ ሁኔታዎችን እናመቻቻለን፡፡ በሙያ ማኅበራት ያልተደራጃችሁ በግል መሥሪያ ቤት የተቀጠራችሁ መምሕራን ከጎናችሁ እንቆማለን፡፡ ሀሳባችሁን እንቀበላለን፡፡ እንድትደራጁም ከጎናችሁ እንቆማለን፡፡ የሴቶች፣ የወጣቶችና የሙያ ማኅበራት ዘርፍ ተጣምረን መሥራት እንዳለብንና ለሚመጣው ምርጫ የእኛ ሚና ከባድና ከፍተኛ ስለሆነ ተሰባስበን እንድንሰራ ጥሪዬን ላቀርብ እወዳለሁ፡፡

*ለቆይታው በአንባቢዎቻችን ስም እናመሰግናለን፡፡*

እኔም በጣም አመሰግናለሁ፡፡

# ‹‹ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በጋራ ለመገንባት ፍቃደኛ ለሆኑ ዜጋዎች በሙሉ በሬ ክፍት ነው›› ኢዜማ

መስከረም13 ቀን 2013ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)




የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የኢትዮጵያ መሠረታዊ ችግሮች በሚመለከት ያለውን እይታ፣ ለችግሮቹ የሚያመላክተው የመፍትሔ ሐሳቦች እንዲሁም ድርጅታዊና ሀገራዊ ዝግጅቱን የዳሰሰበትን መፅሐፍ ‹‹የኢዜማ፣ የኢትዮጵያ መሠረታዊ ችግሮች እይታ፣ የመፍትሔ ሐሳቦች፣ ድርጅታዊና ሀገራዊ ዝግጅት›› በሚል ርዕስ በያዝነው የመስከረም ወር 2013 ዓ.ም አሳተመ፡፡

የመፅሐፉ ተቀዳሚ አላማ ኢትዮጵያን ቀስፈው የያዟት ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና የደኅንነት ችግሮች የትኞቹ እንደሆኑ ማመላከትና ምንጫቸውስ ምንድነው? የሚሉ ጥያቄዎችን መመለስና ለችግሮቹ ኢዜማዊ የመፍትሔ ሐሳብ ማቅረብ መሆኑን ፓርቲው አመላክቷል፡፡ በፓርቲው እምነት የኢትዮጵያ ችግሮች ምንጭ ፖለቲካው ባለፉት 50 ዓመታት የገባበት ቀውስ መሆኑ ተገልጿል፡፡ ‹‹የፖለቲካ ችግሮቹን በፍጥነትና በተጠና እርምጃ በመውሰድና በተወሰነ ደረጃም ቢሆን መቅረፍ ካልተቻለ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የሀገራዊ ደኅንነት ቀውሱ እየከፋ፣ የሞራልና የባህል ዝቅጠቱም እየባሰበት መሄዱ የማይቀር ነው›› ሲል ፓርቲው ስጋቱን አጋርቷል፡፡

ፓርቲው በመፅሀፉ ላይ የመፅሀፉን ዝግጅት ሲጀምር በዋነኛነት አተኩሮ የነበረው ኢትዮጵያን በጠንካራ መሠረት ላይ ማቆምና ማስቀጠል በሚችሉ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የብሔራዊ ደኅንነት ጉዳዮች ላይ እንደነበር አስታውሶ፤ በሀገሪቱ የተከሰተው ዘውግና ሃይማኖትን መሠረት ያደረጉ ግጭቶችና ውድመቶች ተከትሎ ሀገርን የማረጋጋትና የማስቀጠል ጉዳይ ቀዳሚ ጉዳይ ሊሆን ስለሚገባ የመፅሐፉ መግቢያ በዚሁ ጉዳይ ላይ እንዲያተኩር መደረጉን ገልጿል፡፡ ኢትዮጵያን ከዴሞክራሲ ጋር ለማስተዋወቅና ዘመናዊ ሀገር ለማድረግ በርካታ ሙከራዎች መደረጉን ያስታወሰው ኢዜማ፣ ኢትዮጵያ ዛሬም ከዴሞክራሲም ዘመናዊነትም ጋር ብዙም የማትተዋወቅ ሀገር መሆኗን በመጥቀስ ‹‹የምትገኝበት ሁኔታ እጅግ በጣም አሳሳቢ ነው፤ አስጨናቂም ነው›› በማለት ሀገሪቷ የምትገኝበት ሁኔታ ጠቁሟል፡፡ ፓርቲው አስጨናቂና አሳሳቢ ያለውን ሁኔታ ለመሻገርም የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ምሁራን፣ የሀገር ሽማግሌዎችና ሌሎች ባለድርሻዎች በአርቆ አስተዋይነት፣ በትዕግሥት፣ በልባምነትና ከግል ጥቅምና ፍላጎት በፀዳ ስብእና መክረውና ዘክረው ኢትዮጵያን የፍትህ፣ የነጻነት፣ የእኩልነትና የዴሞክራሲ ሀገር የሚያደርግ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ መፃፍ እንደሚገባቸው አስረድቷል፡፡ ይህ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ካልተጻፈ ግን ሀገሪቷ ላይ ፊት ለፊት የተደቀኑባት አደጋዎች ለመሻገር አስቸጋሪ እንደሚሆን ፓርቲው አሳስቧል፡፡

መፅሐፉ በ5 ምዕራፎች የተቀነበበ ሲሆን በመጀመሪያው ምዕራፍ ፖለቲካዊ ጉዳዮች፣ በሁለተኛው ምዕራፍ ምጣኔ ሀብታዊ ጉዳዮች፣ በሶስተኛው ምዕራፍ ማኅበራዊ ጉዳዮች፣ በአራተኛው ምዕራፍ የብሔራዊ ደኅንነት ጉዳዮች ሲዳሰሱበትም በአምስተኛውና በመፅሐፉ የመጨረሻ ምዕራፍ የኢዜማ ድርጅታዊና ሀገራዊ ዝግጅት ተዳሶበታል፡፡

በመፅሐፉ ማጠቃለያ ላይም ፓርቲው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በጋራ ለመገንባት ፍቃደኛ ለሆኑ ዜጋዎች በሙሉ በሩ ክፍት መሆኑን ገልፆ፤ ‹‹ኢዜማን በመቀላቀል ሀገራችንን እናሻግር›› ሲል ጥሪውን አቅርቧል ፡፡



# ‹‹በሁከትና በጉልበት የሚደረጉ ማንኛቸውም እንቅስቃሴዎች ፋይዳ የሌላቸው ናቸው›› ኢዜማ

መስከረም13 ቀን 2013ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

ከመስከረም 25 ቀን 2012 ዓ.ም በኋላ መንግሥት የለም፤ ሕዝብ እና የመንግሥት መዋቅር ለፌደራል እና የክልል መንግሥታት ሊታዘዙ አይገባም በሚል እየተደረገ ያለው ቅስቀሳ ሰላም እና መረጋጋት ከማወክና የዜጎችን ሕይወት አደጋ ላይ ከመጣል የዘለለ ፋይዳ የለውም ሲል የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) አሳወቀ፡፡

ኢዜማ ማክሰኞ መስከረም 26 ቀን 2012 ዓ.ም ‹‹ሰላማችንን በማስጠበቅ እና ቀጣዩ ምርጫ ላይ በንቃት በመሳተፍ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ መሰረት እንጣል›› በሚል ርዕስ ባወጣው መግለጫ ይህንን ቅስቀሳ እያደረጉ ያሉ አካላት ከዚህ ተግባራቸው እንዲቆጠቡና የሀገሪቱ ሰላም እና የዜጎች ደህንነት ተጠብቆ በሰላማዊ መንገድ ችግሮች ተፈተው የውይይት መድረክ ከመምጣት ውጪ በሁከትና በጉልበት የሚደረጉ ማንኛቸውም እንቅስቃሴዎች የማይጠቅሙና አደገኛ መሆናቸውን ሊረዱ ይገባል ሲል ማሳሰቢያውን ሰጥቷል፡፡

በሥልጣን ላይ የሚገኘው መንግሥትም ዘንድሮ ይካሄዳል ተብሎ የሚጠበቀው 6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ እስኪካሄድ ድረስ ሰላማዊ፣ ነፃ እና ፍትሀዊ ለማድረግ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ መስራት እንዳለበት ኢዜማ በመግለጫው ጠቁሟል፡፡ ምርጫው እስኪካሄድ ድረስና የሕዝብ ድምፅ ያገኘው አካል ተለይቶ እስኪታወቅ ድረስም በስልጣን ላይ ያለው መንግሥት የዜጎችን ደህንነት የማስጠበቅ፣ የሀገር ሉዓላዊነትን ማስከበር እና ምርጫውን ነጻ እና ፍትሀዊ ከማድረግ ጋር በቀጥታ ግንኙነት የሌላቸው ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ከማሳለፍና ከመተግበር እንዲቆጠብ ኢዜማ አሳስቧል፡፡

ኢዜማን ጨምሮ በኢትዮጵያ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሙሉ በነፃነት ተንቀሳቅሰው ሃሳባቸውን መግለፅ እንዲችሉ ከዚህ ቀደም የፖለቲካ ፓርቲዎች የተፈራረሙት የቃል ኪዳን ሰነድ መሰረት አድርገው እንዲንቀሳቀሱ ፓርቲው ጠይቋል፡፡ የሲቪክ ተቋማትም የፖለቲካ ፓርቲዎች የተስማሙበትን የቃል ኪዳን ሰነድ እንዲያከብሩ ግፊት እንዲያሳድሩና በጋራ ሊሰሯቸውና ሊስማሙባቸው በሚገቡ ጉዳዮች ላይ ውይይት ማድረክ የሚችሉበትን መንገድ እንዲያዘጋጁ ኢዜማ ጥሪውን አቅርቧል፡፡

ፓርቲው በመግለጫው መደምደሚያ ላይም የኢትዮጵያ ሕዝብ 6ኛው ሀገራዊ ምርጫ ወሳኝ ምዕራፍ መሆኑን ከግምት በመከተት የምርጫውን ሂደት በንቃት እንዲከታተልና ምርጫው ሰላማዊ፣ ነፃ እና ፍትሀዊ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚጠበቅበትን እንዲያደርግ የአደራ ጥሪውን አስተላልፏል፡፡

# ኢዜማ የሕዝብ ግንኙነት መመሪያ እና ደንብ ስልጠና ሰጠ

መስከረም 28 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የኢዜማ ዐብይ ሃሳቦች ፣የኢትዮጵያ ሀገር አቀፍ ምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ፣ የኢዜማ የሕዝብ ግንኙነት ሥራዎች እና የዞን አስተባባሪዎች ሚና እንዲሁም የሕዝብ ግንኙነት ሥራ ጽንሰ-ሀሳብ እና አስፈላጊነቱ ምንድን ነው የሚሉትንና ከህዝብ ግንኙነት ሥራ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሥልጠናዎች በኢዜማ ዋና ጽሕፈት ቤት በመስፍን ወልደ ማርያም (ፕ/ር) መሰብሰቢያ አዳራሽ ተሰጠ፡፡

የኢትዮጵያና የሕዝቧ ጥቅም፣ ሰላም እና ደህንነት እንዲሁም የሀገር ሉዓላዊነት ምንጊዜም ቅድሚያ የሚሰጥ ሲሆን በብዝኃነት (Diversity) የተዋበና የተገመደ አንድ ሕዝብ መሆኑን፣ ማንኛውም ዜጋ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ ወይም በዕድሜ፣ ሳይበላለጥ እኩል መብት፣ እኩል ፍትህ፣ እና በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊና ሌሎችም ሌሎችም መስኮች የመሳተፍ እኩል ዕድል (Opportunity)፣ ሊኖር ይገባል የሚለው ኢዜማ ያስቀመጠው መርህ፣ በስልጠናው ላይ ተካቷል፡፡

እውነተኛ ዴሞክራሲ ለሀገሪቱ ዋና ህልውና እንደሆነ ያልተማከለ የመንግሥት አስተዳደር፣ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤትነትን ወደ ዜጎች በማቅረብ፣ የፖለቲካዊ ግልጽነትንና ተጠያቂነት ባህል በማጠናከር ፣ የመልካም አስተዳደር መሠረት በመሆን፣ ለፈጣን የማኅበራዊና የኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ ሚና እንደሚጫወት ይሄንም ኢዜማ ለመተግበር እየሰራ መሆኑን፣ በተለይ ኢዜማ በተልዕኮው ሰፊ የሕዝብ መሠረት ያለው ፓርቲ በመገንባት እና በዴሞክራሲያዊ የምርጫ ሂደት የመንግሥት ሥልጣን ባለቤት በመሆን የፓርቲውን መርሆች መሠረት ያደረጉ የዕድገት፣ የልማት እና የሥልጣኔ ፖሊሲዎችን በመቅረጽና በማስፈጸም በራዕዩ ላይ የተቀመጠችውን ዘመናዊትና ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ እንደሚተጋ ተጠቅሷል፡፡

ኢዜማ በሕዝብ ግንኙነት በኩል የተለያዩ መረጃዎችን ለህዝብ ተደራሽ ለማድረግ የህትመት፣ የብሮድካስት እንዲሁም ማኅበራዊ ሚዲያን በስፋት የሚጠቀም መሆኑ ይታወቃል፡፡ የወረዳ ሕዝብ ግንኙነቶች ሚዲያዎችን ሲጠቀሙ የኢዜማ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ እሴቶችን ማሰብና መተግበር የፓርቲውን አላማና መርህ ተከትለው መጓዝ እንዳለባቸው በማሳወቅ፣ የዞንና የምርጫ ወረዳዎች ማኅበራዊ ሚዲያ ሲከፍቱ በቅድሚያ ለወረዳው ሕዝብ ግንኙነት በማሳወቅ መክፈትና ለማዕከል በማሳወቅ መጠቀም እንዳለባቸው የኢዜማ ማኅበራዊ ሚዲያ የሥነ - ምግባር ደንቦችና መርሆች የሚባሉት ለሰልጣኞቹ በዝርዝር ተብራርቷል፡፡

የኢዜማ በማዕከልም ሆነ በምርጫ ወረዳዎች የሚተዳደሩ ማኅበራዊ ሚዲያዎች በኢዜማ ማንኛውም ገፆች ውስጥ ከፓርቲው ጋር ተያያዥነት የሌላቸውን ማስታወቂያዎችን እና ፖስቶችን መለጠፍ የማይችሉ መሆኑን በስህተት ከተለጠፉም አስተዳዳሪዎቹ ወዲያውኑ ማጥፋት እንደሚገባቸው፣ የኢዜማ የዕለት ዕለት እንቅስቃሴ የሚያሳዩ በማኅበራዊ ሚዲያ ገፆችን ስራዎችን ማቀላጠፍ፣ ስለ ፓርቲው ቶሎ ቶሎ መረጃዎችን ለህዝብ ማድረስ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊነት እና ግዴታ መሆኑ በስልጠናው ወቅት ተገልጿል፡፡

ኢዜማ ያዘጋጀው ስልጠና ዋና አላማ በታማኝነት የሚሰጡ መረጃዎች ኃላፊነት በተሞላው መልኩ መጠቀም እንደሚገባ ቀጣይ ሀገር አቀፍ ምርጫ ሁሉም የኢዜማ መዋቅር ተመሳሳይ የሚዲያ አጠቃቀም እንዲኖራቸው ለማድረግ ታስቦ እንደሆነ ታውቋል፡፡